# የጠገዴ ጉዳይ
(ባበይ ክንፉ)

ባበይ ክንፉ እባላለሁ ፣ የተወለድኩት በ1971 ዓ.ም. (ሁሉም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው) ጠገዴ አረማ ጎርጊስ ቀበሌ፣ መልክአ ምድሯ ውብ፣ ማራኪ በሆነችው ጠገዴ ደቃ አጋሮ ነው። አገሬ ጠገዴን በጣም እወዳለሁ፣አቀማመጧንና የአየር ጸባዩዋን ሳስታውስ በትዝታ እኳዛለሁ። ጠገዴ በሶስት አየር ንብረት ክልል ትገኛለች፣ ደጋማ ፣ወይናደጋማና፣ ቆላማ ሲሆኑ ደጋና ወይናደጋማው ክፍል በተራራና በገደላ ገደል የተከበበ በጣም ደስ የሚል ማራኪ ገጽታ ያለው አገር ነው። ሸንተረሮቿ፣ ወንዞቿ ፣ ሸንጥሮቿ፣ ሜዳዎቿ፣ ገደሎቿ፣ እንዲሁም ረጃጅም ፏፏቴዎች የሚበዙባት ውብ ሃገር ናት። በውስጧዋ ብዙ አንጡራ ሃብቶችን የያዘች መልካም አገር ናት። ለቱሪዝም፣ ለግብርና፣ ኢንዱስትሪ ያመቸች አገር ናት። ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የተፈጥሮ ፍል ውሃም አላት።
ጠገዴን ለማየት ወይም ለመውጣት በትላላቅ ገደላማ የተከበበች ከመሆኑዋ አንጻር እግዚአብሄር ለመኖሪያ ስለባረካት መውጫ መግቢያ በተፈጥሮ በር አበጅቶላታል። እነዚህም በሮች ኬላዎች

በዛና፣ አቀው ጊላ
በደቅ አጋሮ፣ አውሻላ
በአረማ፣ ሙልጭ
በናዴር፣ ጎርዞ
በአበተልባ፣ መንኮሎ
በሳርና፣ ጭልቁዋና
በተዛሪፋ፣ ክራ

እነዚህ እኔ የውጣኹና የወረድኩባቸው ሲሆኑ በአጠቃልይ ጠገዴ 18 መውጫ መውረጃ አሉዋት። ከማራኪነታቸው የተነሳ ሁሌ ስወጣና ስወርድ ድካም አይሰማኝም ነበር። ብዙ ሰው እነዚህን መውጫን መግቢያዎችን ሲያማርር ሰምቼ አላውቅም። ነፍስ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን አቀበቱን ለመውጣት ፣ቁልቁለቱን ለመውረድ በጣም እችኩል ነበር። በሚያምሩ ወፎችና እነሰሳት ድምጽ ታጅቤ እጓዝ ነበር። አቀበቱን ስጨርስ ከሞቀው ወደቀዝቃዛው ስዘልቅ ቤቴ መድረሴ እየተሰማኝ መንፈሴም ይታደሳል፣ ድካሜም ይለቀኛል ። በተለይም በአቀው ጊላ ስዘልቅ የሚሰማኝ ስሜት ለየት ያል ነው። የጭላዳዎቹ ትቢትና ጩኸት ፣ ደስ የሚል መንፈስ ያሳድርብኝ ነበር።

በጠገዴ ብዙ ደግና ክፉ ነገሮችን አይቻለሁ። ያሰደገኝ አያቴ ታታሪ ገበሬ ስለነበር ስራ ወዳድነትን፣ ድፍረትን፣ የሰው ፍቅርን፣ እንዲሁም መከራ መቋቋምን እንድችል አድርጎ አሳደገኝ። የመጨረሻ ልጅ ነኝ። ፈጣንና ጠንካራም ስለነበርኩኝ አምስት አመት ከሞላኝ ጀምሮ ከስራ ተለይቼ አላውቅም። የመጀምሪያ ስራዬ ከብቶችንና ፍየሎችን አንድ ጋር አድርጌ በእረኝነት እሰራ ነበር። የክረምት ብርዱንና የበጋውን ሙቀት ተቋቁሚ በደስታ እሰራ ነበር። ለአያቴ ያለኝ ፍቅር ከፍ ያለ ነው። አያቴም ፍጥነቴን፣ ማስተዋሌንና የማስታዋስ ሁኔታዬን በተደጋጋሚ ያደንቅ ነበር።

አያቴ በአካባቢው በሚኖረው ህዝብ እውቅና ያላው ሰው ነው። አማርኛ፣ግዕዝና ትግርኛ ይናገር ነበር። የባህል መዳኒት አዋቂ ሲሆን የታወቀ ወጌሻም ነበር። ሬድዮ ከአጠገቡ አይጠፋም ነበር። ከሬዲዮ ያገኘውን መረጃና ዜና ለመንደርተኛው ያደርስ ነበር።

በስድስት ዓመቴ ከአያቴ ጋር ስንጫወት ለመሆኑ የዛሬ ሶስት ዓመት (የሶስት ዓመት ልጅ እያለሁ ዓያቴ ምርር ብሎ ሲያለቅስ አይቼ ስለነበር ) በ1974 ዓም በቅዱስ ዮሓንስ ቀን ለምንድነው ምርር ብለህ ያለቀስከው ብዬ ጠየኩት። ዓያቴ ይህንን ሲመልስልኝ ሁኔታውን በማስታወሴ በመገረም ደጉ

አባቶችንና ንጉሳችን ጃንሆይ በጉልበት ከስልጣናቸው ስለወረዱ ነው አለኝ። ልጁ ዘመኑ ከእንግዲህ የእልቂት ነው የሚል የሚያሳዝንና የሚያስደነግጥ ወሬ ነገረኝ። እኔም ለጓደኞቼ ይህንን አስደንጋጭ ዜና በመናገሬ መቋቋም ያቃታቸው ጓደኞቼ ለፍርሃት ተዳርገው ነበር።
ንጉሡ በተገደሉ በአራተኛው ዓመት (1979) እኛ አካባቢ የነበረው ሕዝብ ከብት ያለው ከብቱን እየሸጠ ከብት የሌለው እየሰረቀ መሳሪያ መግዛት ጀመረ። እኛ ቤት ብቻ ስምንት መሳሪያዎች ክላሽና አብራራውን ጨምሮ ገዝተን ነበር። መሳሪያ የሌለው ሰው እየተናቀ መጣ። ሱሪ ያጠለቀ በሙሉ መሳሪያ መያዝና መታየት ከመጀመሩም በላይ መረበሹ በግልጽ ይታይ ነበር። በዛን ሰሞን አዴት ከምትባል የጠገዴ ቆላማ ምድር ለመጀምሪይ ጊዜ ኢሐፓ የምትባል ታጣቂ የሰው ሃብት ንብረት ዘራፊ መጥታለች እየተባለ ይነገር ጀመር። በእኛ የደረሰብን በእናንተ ላይ እንዳይደርስባችሁ የሚል መልእክት በየቤተክርስቲያኑ ይተላለፍ ነበር። ኢሓፓ ቆላው ላይ ያደረሰችውን ዝርፊያ በመመልከት ደጋማው የጠገዴን ምድር እንዳይረግጧት የሚል አዋጅ ተነገረ። ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ከኢሓፓ ጋር ብዙ መተላላቅ ሆነ። ሕዝቡ አናስገባም ብሎ ቢዋጋም የኢሓፓ ኃይል በርትቶ አካባቢውን በኢሓፓ ቁጥጥር ስር ሆነ።

ኢሓፓ ልታሸንፍ የቻለችበት ዋነኛው ምክኒያት ጠገዴ ውስጥ የነበሩ የጠገዴ ድሖች መሳሪያ ከኢሓፓ ለማግኘት ሲሉ የሓገሬውን ሚስጥር ስለሰጡ ነው። ሆኖም ኢሐፓ ወይናደጋማው ጠገዴ ከገባች በኃላ ዓላማዋን ማስረዳትም ሆነ ሕዝቡን መያዝ አልቻለችም ነበር። ሕዝቡም እያደፈጠ ከመግደል አላቆመም ነበር። ከአንድ ዓመት በኃላ ኢሓፓ ከሕዝቡ ጋር ተደራድራ አገሩን ለቃ ለመሄድ ወሰነች። ሕዝቡም በዚህ ተስማምቶ ዘግቶት የንበረውን መውጫ በር ከፍቶ አሰናበታት። ከጥቂት ወራት በኃላ በጠገዴ ደጋማው ክፍል ኢዲዩ የሚባል ኃይል መጣ። ኢዲዩ ከገበሬው ጋር በመተባበር የተረፈውን የኢሓፓን ወንበዴ ከደጋውና ከወይናደጋው ጠራርገው አስወጡ።

ህዝቡም ኢድዩን ለግዜው የተቀበልበት ምክኒያት ዋነኛው በኢሓፓ በደረሰበት የንብረት ዝርፊያ፣ የቤተሰብ ድፍረት፣ ህገወጥ አስገባሪነት ሰልችቶት ስለነበር ነው። ከጥቂት ግዜ በኃላ ኢዲዩ ደግሞ በተራው ገበሬውን ማዘዝና ስራ ማስፈታት ስላበዛበት መቃቃር ጀመሩ። አንድ ዓመት በኃላ ያለምንም ደም መፋሰስ ቦታውን ለቀው ወደ ሁመራና አብደራፊ ተሸኙ። ይህም ሆኖ ኢሓፓ የሽፍትነት ስራዋን ቀጥላ አካባቢውን ትረብሽ ነበር። እንደዚህ እየታመሰ የከረመው የጠገዴ ሕዝብ በ 1981 ሃምሌ ወር ላይ ተጋዳላይ ሕዝብ ትግራይ የምትባል ደጋማውን ጠገዴን ሙሉ በሙሉ ከይት መጣች ሳትባል መያዟ ተሰማ። በጥቂት ወራት ውስጥ የጠገዴን ወይናደጋማውን ክፍልና የትውልድ ቦታዬ የሆነውን ምድር ለመጀምሪያ ግዜ ረገጠች። ተጋዳላይ ሕዝቢ ትግራይ (ተሐት) ነኝ ያለችው ለስለስ ብላ፣ ጠገዴን መስላ፣ ጠላጥህ ጠላቴ ነው፣ ወዳጅህ ወዳጄ ነው ብላ ሰዉን አግባብታ በቀላሉ ሕዝቡ ልቦና ውስጥ ገባች።

ተሐት በምታደርገው ስብሰባ ሁሉ ከህዝብ የተወለድኩ የሕዝብ ልጅ ስለሆንን አብረን ጠላት የሆነውን ደርግና ኢሓፓን ማጥፋት ነው ብላ ታስተምር ነበር። ኢሓፓ ከህዝብ ቀማኝነትና ለሕዝብ ክብር ያማትሰጥ ድርጅት ነች እያለች መስበክ ጀመረች። ደርግንም በሚመልከት ሰው በላ፣ ሃይማኖት የሚይስክድ፣ ክርስትና እንዳትነሱ የሚከለክል፣ የሰው ሕብትና ንብረት የሚዘርፍ ቀማኛ እያለች ማስተማር ጀመረች። የጠገዴ ሕዝብ በሓይማኖቱ ሲመጡበት ድርድር ስለማያውቅ ደርግ የሚባል አረመኔ አገራችንን እንዳይረግጥ በማለት ሙሉ በሙሉ የተሓትን ዓቋም ተቀበለ።

እሁድ ለት አማጋ የሚባል የከብቶች ማረፊያ ቦታ የተሓት ሰዎች መጥተው አያቴ ትግሪኛ እንደሚናገር ጠየቁኝ። ከመሄዳቸው በፊት አያቴን ልናናግራቸው እንፈልጋለን የሚል መልዕክት አድርስ ብለውኝ ሄድኩ። መልዕክቱንም አድርሼ አያቴም ፍቃደኛ ሆኖ ኣማጋ ላይ በማግስቱ ተገናኙ። አያቴን ለማግኘት የፈለጉበት ምክንያት ቤተክርስቲያን መጥተው ከህዝቡ ጋር መተዋወቅና መቀራረብ ስለፈለጉ ነበር። አያቴም በዚህ ሃሳብ ተስማምቶ ወደ ቤተክርስቲያን በሚቀጥለው ሰንበት ጋበዛቸው። የተለመደውን የፕሮፓጋንዳ ትምህርታቸውን ሰጡ። ከነዚህ ትምህርታቸው ውስጥ የማስታውሰው ለሕጻናቶች የሚገባውን እንክብካቤ አድርጉ የሚል ነበር። ሴት ልጆቻችሁን በልጅነታሁ አትዳሩ፣ታዳጊ ሕጻናቶችንም ከዕድሚያቸው በላይ የሆነ ከባድ ስራ

አታሰሯቸው የመሳሰሉት ምክሮች በተለይም በእናቶች በኩል ተቀባይነት አገኙበት። በተጨማሪም ተቀባይነትን ያስገኘላቸው የሰውን ሐብትና ንብረትን ማክበርና አለመዝረፋቸውና እንደውም አልፈው ተርፈው ኢሐፓ የዘረፈባችሁን እናስመልሳለን በማለት ለሕዝቡ ተስፋ በመዝራት ከሕዝቡ የሚፈልጉትን ድጋፍ ሙሉ በሙሉ አግኝተዋል።ከዚህ አንጻር ብዙ የአካባቢው ወጣቶች በገፍ ወደ ተሐት መቀላቀል ጀመሩ። ተሐት ሙሉ በሙሉ አካባቢውን መቆጣጠር ቻለች። ከሕዝቡም ጋር በማበር ኢሐፓ ያለችበትን ቆላማውን አካባቢና ግጨው ተራራን፣ ኢሐፓ ትኖርበት የነበረውን ቦት ታላቅ መስዋትነት በመክፈል ቦታውን በቁጥጥሯ ስር አዋለች። ኢሐፓ ወደ ቋራ መተማ ሸሸች። ጠገዴ ሙሉ በሙሉ ከቆላ እስከ ደጋ በተሐት ቁጥጥር ስር ዋለች።

በዚህ ሰዓት ነበር እኔም በነሃሴ ወር ላይ 1984 ኢሓፓ የመሸገችበትን ቦታ ታውቃለህ ተብዬ ምራ ተብዬም እየመራሁ እያለ ኢሐፓ ቀድማ ሰምታ ስለንበር በር ዘግታ ትጠብቅ ነበር፣ በተከፍተው ተኩስ እግሬን ተመትቼ በ1984 ዓመቴ አካለ ስንኩል ሆንኩኝ። ከ 1984 እስከ 1986 የጠገዴ ሕዝብ ከተሐት ጋር ያለምንም ችግር ቆየ። ቀስ በቀስ ጸባያቸውን እየቀየሩ መጡ። በሕዝቡ ተቀባይነት የሌላውን ሕዝብን የሚያስጨንቅ ትዕዛዝና ግዴታ መስጠት ጀመረች። ወደ ደርግ ና ወደ ኢሐፓ የገቡትን ወገኖቻችሁንና ዘመዶቻችሁን አስመልሱ በማለት ትዕዛዝ አስተላለፈች።ይህ ትዕዛዝ ለጠገዴ ሕዝብ በጣም ፈታኝ ነበር። ሕዝቡም ይህንን ማድረግ አንችልም ብሎ በመመለሱ ለከፍተኛ ግፍና በደል ትዳርገው ጀመር። ይባስ ብሎም ከየካቲት 15 አስከ መጋቢት 19 1984 በተካሄደው ስብሰባ ተሐት አዲስ ያለችውን ሐሳብ ይዛ ብቅ አለች። ሐሳቡም ከዛሬ ጀምሮ ጠገዴ ተጠሪነቱ ለጎንደር ሳይሆን ለትግራይ ነው ብላ ሕዝቡን አስደነገጠች። ሕዝቡም በዚህ ዕለት ከፍተኛ ውዝግብ ያስነሳ ጥያቄና ሐሳብ በማንሳት አልቀበልም አለ። ተሐት ግን ይህ ስውር ስራውን በግድ ትቀበላላችሁ በማለት ሲያዋክቡት የጠገዴ ሕዝብ አቋሙን ግልጽ በማድረግ አይሆንም በማለት ተሐት የጠራችውን ስብሰባ ረግጠው በመውጣት ሆድና ጀርባ ሆኑ።

ስብሰባው ባለቀበት ማግስት መጋቢት 27 የአካባቢው ሕዝብ መድሐኒያለም ንግስ በዓልን ለማክበር ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ከዛሬ ጀምሮ ተሐት ያለኛ ፈቃድ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳትገባ ተወሰነ። በጣም አስተዋይ የነበረች የትግራይ ተዋልጅ የፕሮፓጋንዳ ሓላፊ የነበረችው ታጋይ ምሕረት ወልደአብ ሕዝቡን ሓሳብችሁን ተቀብዬአልሁ ያለናተም ፈቃድ የሚሆን ነገር የለም በማለት ሕዝቡን አረጋጋችው። ሓሳባችሁን ለአለቆቼ አሳውቄአለሁ አለች።

ጠገዴ፣ ደባስ ክንድሽ የሚባል ስፍራ ላይ ከደርግ ጋር በተደረገው ውጊያ ምሕረት ወልደ አብ መገደሏን ሰማን። አሟሟዋታ ሲታወቅ ግን ሆን ተብሎ ለጠገዴ ሕዝብ ደግ አመለካከት ስለነበራት እሷንም ከቦታው አንስተው ሌላ ሰው ለመሾም ስለፈለጉ እሷን ጦርነት ላይ እንደሞተች አስመስሎ አጠፏት። ከዚያም መርዞ በሚባል አረመኔ ወረዳው መተዳደር ጀመረ። መርዞ ከተሾመ 1984 በሓላ የጠገዴ ሕዝብና ተሓት ጠላት ሆኑ። ከ 1984 እስከ 1988 ድረስ ጠገዴ ወደ ትግራይ ይካለላል የሚለው ሃስብ ተነስቶ አያውቅም ነበር። በ1993 ያለምንም ሕዝብ ተሳትፎ ኢትዮጵያን በሙሉ ስላሸነፍን በማን አልብኝነት ወደ ትግራይ ተጠቅልላችኋል ተባልን። የሚያሥነው ነገር ቢኖር አንድ የጠገዴ ጎንደር ለመድረስ ስድስት ስዓት ይፈጅበት የነበረው ቀርቶ ሁለት ቀን ተኩል ተጉዘህ በማታውቀው ቋንቋ ጉዳይህን መቀሌ ላይ አመልክት ተባለ።

በዚህም ትዕቢት በተሞላበት ውሳኔ የተነሳ ጉዳዩን መቀሌ ላይ ለማስፈጸም የጠገዴ ሕዝብ ሲጉላላ እንሆ 25 ሆነው። ይሄ በሕዝብ ያልታቀፈና ያልተደገፈ ሴራ ቀኑ ሲደርስ እንደሚፈርስ አልጠራርጥርም። በዚህም አጋጣሚ ለማሳሰብ የምፈልገው ከሌላ ኢትዮጵያ ክፍል የወጣችሁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲገነዘቡልን የምጠይቀው የጠገዴና የወልቃይት ሕዝብ ይህንን የመሰለ ስቃይ በራሱ ላይ እንዳላመጣና እንደማንኛውም ሰው በየዋህነት መታለሉን ፣ በትግራይ ለምትኖሩ ውንድሞቻችን ደግሞ የጠገዴና የወልቃይት ሕዝብ ስቃይ የናንተም ስቃይ መሆኑን አትዘንጉት። ሁላችንም ለብዙ ዘመናት ተዋደንና ተጋብተን የኖርነው ኢትዮጵያ በምትባለው ዋርካ ስር መሆኑን አንዘንጋ።